ማዉጪያ

1) ታሪክ ……………………………….. ……………………………………….ገጽ 2
1ሀ) ከክርስቶስ ልደት በፊት (ዓዓ) በጥቂቱ ……………………………..ገጽ 2
1ለ) ከክርስቶስ ልደት በኍላ (ዓም) በጥቂቱ …………………………… ገጽ 2

2) መግቢያ •ህዝበ-ሕግ -[በሃሳጥሮ] ………………………………..ገጽ 4
2ሀ) ስጦታ ……………………………………………………………….ገጽ 4
2ለ) ቋንቋና ፊድል ……………………………………………………...ገጽ 4
2ሐ) "ህይውት: ነጻነት: መተዳደሪያ" ሊነጣጠሉ የማይችል ተፈጥሯዊ ተሰጥኦ ናቸዉ::. ገጽ 4
2መ) ማንኛውም ሰዉ የመናግር ነጻነት አለዉ:: …………………………….… ገጽ 4
2ሠ) የጠቅላይ ግዛት: አዉራጃ: እና ወርዳ: ወይም ቀበሌ ስም በዘር ወይም በጎሳ ስም አይጠራም:: ……………………………………………………………… ገጽ 4

3) አወቃቀር •ህዝበ- ሕጋዊ ሦስት ክፍል ያለዉ መንግሥት አወቃቀር• ……………..ገጽ 4
3ሀ) ክፍል 1. የሕግ አዉጪ ጉባዕዔ: ጉባዔዉ የህዝብ ወኪሎች (ህወ) እና የጠቅላ ግዛት ወኪሎች (ጠወ) …………………………………………………………………ገጽ 4
3ለ) ክፍል 2. ሥራ አስፈጻሚ ክፍል: ፕሬዚዳንት: ምክትል ፕሬዜዳንት: እና ሚኒስትሮች..ገጽ 5
3ሐ) ክፍል 3. የዳኞች ክፍል ......................................................................................ገጽ 5

4) ክፍሎቹ እርስ በርስ ይቆጣጠራሉ:: ……………………………………………ገጽ 5

እነሆ: ማንም ሰዉ በሕግ ፊት እኩል ነዉ:

5) መደምደሚያ …………………………………………………………… ገጽ 6

የቃላት ትርጉም ....................................................................................................... ገጽ 7

መቅድም:

ታሪክ: ኢትዮጵያ ረጂም ታሪክ አላት:: አዲስ ተፈጣሪ አይደለችም::

ኢትዮጵያ ረጂም ታርክ አላት:: የራሷ ፊደልና ዘመን አቆጣጠር አላት::

1ሀ) ከክርስቶስ ልደት በፍት (ዓዓ) በጥቂቱ:

1 ሀ1) ወደ 10,000 ዓዓ ገደማ:

ከ12 ሺህ ዓመት በፊት ኢትዮጵያዊያን ወደ ቅርብ ምሥራቅ ሄደዉ አረብኛ: ሳባዊ እና የሴም ቋንቋዎች ግዕዝ ና እብራይስት ተመሰረቱ::

1ሀ2 ወደ 950 ዓዓ ገደማ:

የቤተ እስራኤል ሰዎች (በብሉይ ኪዳን አማኞች) ኢትዮጵያ መጡ::

1ለ) ከክርስቶስ ልደት (ዓም) ታርክ በጥቂቱ::

1ለ1) ወደ 340 ዓም ገደማ:

ዓፄ ኤዛና ከመርዌ (አሁን ሱዳን ዉስጥ) እስከ የመን ይገዙ ነበር:: አዲስ ኪዳንን ለመቀበል: ዓፄ ኤዛና አቶ ፍሬምናጦስን አሌክሳንድሪያ ላኩ:: የአሌክሳድርያ ፓትሪያርክ ፍሬምናጦስን አቡነ ሰላማ ብለዉ ወደ አክሱም መለሷቸዉ:: የኢትዮጵያ ሊቃዉንት ሃይማኖት ኦርቶዶክስ ክርስቲያን ሆነ::

1ለ2) እስከ 550 ዓም ገደማ: ኢትዮጵያ በዓለም ከነበሩት አራት ኃያላን አገሮች አንዷ ነበረች::

ወደ 550 ዓም ገደማ: የፐርሺያ ነገሥታት (ሳሳኒዲ ሥርወ መንግሥት ) ወታደር ወደ ግብፅ ከላኩ በኋላ: የአክሱም ሥርዎ መንግሥት ወደ ደቡብ ሄደ:: የኢትዮጵያ ሊቃዉንት ተከዜን ተሻግረዉ ከአክሱም ወደ ደቡብ ሄዱ:: እነ ቅዱስ ያሬድ ጎንደር ሄዱ::

ወደ 550 ዓም ገደማ: መሐንዲሱ ባኩም ደቡብ አረብ ሰላጤ: የከአባን መሳለሚያ አደሰ::

1ለ3) ወደ 590 ዓም ገደማ: ነብዩ ሞሐመድ ዘመዶቻቸዉንና ተከታዮቻቸዉን በሰላም ይኖሩ ዘንድ ወደ ኢትዮጵያ ሄደዉ ጥገኝነት እንዲጠይቁ አዘዙ::

1ለ4) 1170 ዓም ገደማ: ኤንጂኒየሩ ቅዱስ ዓፄ ላሊበላ (የዛግዌ ስርዎ መንግሥት) በላስታ የጊዮርጊስን ገዳም አሠሩ:: ገዳሙን ከምድር ስፈፍ ጀምረዉ ወደ ምድር ድንጋይ እያስቆፈሩ ሲያሠሩት:

1ለ4ሀ) የድንጋይ ፍርስራሽ ከገዳሙ ወደ ሌላ ቦት የሚወስድበት ቦይ አሠሩ::

1ለ4ለ) የሠራተኞች ሽንትና መጸዳጃ የሚይልፍበት የተከደን ቦይ እሠሩ::

1ለ4.ሐ) የገዳሙ ቀሳዉስትና ምእመን መጸዳጃ በተከደነ ቦይ መሄጃ አሠሩ::]

1ለ5ሀ) ዓፄ ምንሊክ 1882 ዓም: ጥቅምት 25 የንጉሠ ነገሥት ሥልጣን ፈቅደዉ አከበሩ:: "በታህሳስ ወር ...ትግሬ ለመዝመት አድስ አበባን ለቀቁ::" 1888 ዓም : የካቲ 23 አድዋ ላይ የጣልያንን ወራሪ ገጥመው ድል አደረጉ::

1ለ5ለ) 1888 ዓም ዓፄ ምንሊክ አድዋ ከጣሊያን ጋር ሲዋጉ: ህዝቡ ለአልጋዉ ጽናት ተዋጋ:: [አልጋዉ ህዝብ ነዉ:: የህዝብ ሠራዊት ከያለበት ወደ እድዋ እንዲዘምት ዓፄ ምንሊክ ብዙ እቅድ (lሎጂስቲክስ: logistics) ተጠቅመዉ ነበር::]

1ለ6) ከ1967 ዓም ከደርግ ጊዜ እስክ እሁን ወንጀለኞች ህዝብን ንቀዉ ሥልጣን ያዙ:: በነኝህ ወንጀለኞች ድንቁርና ምክንያት ኢትዮጵያ የባህር ወደቦቿን ከስዋኪን እስክ ሞጋዲሽ ማስመለስ እንዳትችል ደንቃራ ሆኑ:: በአግባቡ እና በህዝብ ፈቃድ አልሠሩም:: ባለፈዉ አምስት አመት ወንጅል እጅግ በጣም በዛ:: ከ2015 ጀምሮ: ከወንጀለኞች ለመዳን ህዝቡ ዉጊያ ገጥሞ ፋኖ ኀለበተ::

እላይ በታሪከ ከ 1ሀ እስከ 1ለ6 የተጠቀሱት እንደሚገልጹት ወንጀለኞችን ለማዉደም በ "ህዝበ-ሕግ" (ካንስቲቱዩሺን ) መስረት ለመተግበር ባለሥልጣናት ሁሉ መሓላ ማድረግ አለባቸዉ:: ፋኖም ህዝበ-ሕጋዊ ( ዴሞክራሳዊ) መንግሥት እቋቁሞ ምምራት ይጀምራል::

2) መግቢያ

2ሀ) ስጦታ:
እኛ ኢትዮጵያዊያን በአብሮነት ለመኖር: በኢኮኖሚ: በጥበብ እና በእዉቀት ለማደግና ወንጀለኞችን ለማስወገድ የሚከተሉትን ደምቦች ለራሳችን እና ለትዉልድ ሰጥተናል:: ይህ ስትጦታ በኤርትራ: በስማሊላንድ: እንዲሁም በሱማሊያ ለሚኖሩ ወንድምና እህቶቻችን ክፍት ነዉ::

2ለ) ቆንቋና ፊድል:
ምንም እንኳ የግለስብ እና ስብስብ የፈቀደዉን ቋንቋ የመጠቀም መብቱ ቢከበርም: የኢትዮጵያ የጋሮሽ ቋንቋ አማርኛ ነዉ:: የሚጻፈውም በግዕዝ ፍፊደል ነዉ::

2ሐ) "ህይውት:ነጻነት: መተዳደሪያ" ሊነጣጠሉ የማይችል ተፈጥሯዊ ተሰጥኦ ናቸዉ::
(Life, liberty, and livelihood are inalienable natural state.)

2መ) ማንኛውም ሰዉ የመናግር ነጻነት (freedom of speech) አለዉ:: ሰለዚህ: የግለሰብ ጋዜጦኞች መብት በህዝበ-ሕግ የተጠበቀ ነዉ::

2ሠ) የጠቅላይ ግዛት( province): አዉራጃ: እና ወርዳ ወይም ቀበሌ ስም በዘር ወይም በጎሳ ስም አይጠራም::

3) አወቃቀር:

ከ2ሀ እስከ 2ሠ የተጠቀሱትን ነጥቦች በግብር ለማሳካት: እርስበርስ ተቆጣጣሪና ተመዛዛኛ የሆነ ባለሦስት ክፍል መንግሥት ይኖረናል::

3ሀ) ክፍል 1. የሕግ አዉጪ ጉባዔ (Congress):: ጉባዔዉ ሁለት ክፍሎች ይኖሩታል:: እነሩስም: የህዝብ ወኪሎች (ህወ: House of Representatives) እና የጠቅላ ግዛት ወኪሎች (ጠወ Senate) ናቸዉ::
[የህዝብ እና የጠቅላይ ግዛት ወኪሎች በህዝብ ተመርጠዉ የወኪሎች ጉባዔ ይሆናሉ (ክፍል1)]

3ለ) ክፍል 2. ሥራ አስፈጻሚ ክፍል (Executive):: ፕሬዚዳንት: ምክትል ፕሬዜዳንት: እና ሚኒስትሮች አሉት::

3ለ1) ፕሬዜዳንት ምክትል የሚሆነውን ስዉ ወስኖ: ፕሬዜዳንቱና ምክትል ፕሬዜዳንቱ ከሌሎች ተወዳድረዉ በኢትዮጵያ የህዝብ ድምጽ ብልጫ ለአራት አመት ይመርጣሉ::
[ፕሬዜዳንት የሚመረጠዉ: 1. ኢትዮጵያ የተውለደ: 2. እድሜዉ ከ 35 እስክ 75 የሆነ:
3.ከዚህ በፊት ህዝብ-ሕግን ለማፍርስ ያልጣረ ነዉ::]

3ለ2) የከቢኔት ሚኒስቴሮች: ፕሬዜዳንቱ እጩዎች መርጦ: የ ጠወ ጉባዔ ከ 100 ወኪል 60 እጁ በላይ የይሁንታ ድምጽ ሲሰጥ እጩዎቹ የካቢኒት ሚኒስቴሮች ሆነው ይሾማሉ::

3ሐ) ክፍል 3. የዳኛ (Judiciary ) ክፍል:: ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞችና እና በተዋረድ በየመስትዳድሩ ክፍል ዳኞች ይኖሩታሉ:
[ፕሬዜዳንቱ እጩዎች መርጦ: በዳኝነት እንዲያገለግሉ የ ጠወ ጉባዔከ 100 ወኪል 60 እጁ በላይ የይሁንታ ድምጽ ሲሰጥ እጩዎቹ ዳኞች ሆነው ይሾማሉ:]

3መ) ከመንግሥት መሥሪያ ቤት ዉጪ አገልጋይ ክፍል መረዮች የሚሆኑትን እጩዎች ፕሬዜዳንቱ አጭቶ የ ጠወ ጉባዔ ከ 100 ወኪል 60 እጁ በላይ የይሁንታ ድምጽ ሲሰጥ እጭዎቹ የመሥሪ ቢት መርዮች ሆነው ይሾማሉ:
ምሳሌዮች:
3መ1) የመከላከያ ወታደር እዛዥ
3 መ2) የህዝብን የኢኮኖሚ ዕድገት የሚቆጣጠር የመሃከላዊ ባንክ መሪ (Chairman of National reserve Bank)
3መ3) የአገር ነዋሪና ድርጂት ፍትህ እንዲያገኝ ሙሉ አገባብ  የትስጠዉ የፍትህ እና ርትዕ ቢሮ አዛዥ ጠበቅ (Attorney General - Department of Justice)

3መ..).. ወዘተርፈ

4) ክፍሎቹ እርስ በርስ ይቆጣጠራሉ:

4ሀ. ህግ ማውጣት

የ (ክፍል 1) ጉባዔ መክሮ ያቀረበበው ደምብ በፕሬዚዳንቱ (ክፍል 2) ሲያጸድቅ ሕግ ይሆናል::

4ለ. ህግ ጣሽ ባለሥልጣን
ፕሬዜዳንቱ: ምክትሉ ( ክፍል2) ወይም ፕሬዜዳንቱ አጭቶ ያሾማቸዉ ሰዎች የህወ ጉባዔ (ክፍል 1) በድምጽ ብልጫ ሕግ የጣስ ሰዉ መሆንን ሊያብሥር ይችላል (impeached) :: ያንን ህወ ሕግ የጣሰ ነዉ (impeached) ያለዉን ባለሥልጣን ጠወ ከ 100 ወኪል 60 እጁ በላይ የይሁንታ ድምጽ ሲሰጥ ከተስማማ ተከሳሹ ወንጀለኛ ሆኖ (convicted) ከሥልጣን ይባረራል::

4ሐ. (ክፍል 1) ወይም ህዝበ-ሕግ ሳይፈቅድ
ፕሬዜዳንቱ ሊተገብር አይገባም:: ቢሠራቸዉም: ጉዳዮች ሕጋዊ አይደሉም:: የሚከትሉት ምሳሌዮች እንይ::

4ሐ1) ፕሬዚዳንቱ ( ክፍል 2) ህወና ጠወ (ክፍል 1)  ያልተመነዉን ገንዘብ ለምንም ጉዳይ አያዉልም::

4ሐ2) ፕሬዘዳንቱ (ክፍል 2) ከህወ (ክፍል 1) በድምጽ ብልጫ ይሁንታ ሳያገኝ ከሌላ አገር: የአገሮች ስብስብ: ወይም የሌላ አገር ድርጂት: ወይቶች ስምምንት: ስጦት ወይም ሽልማት: አያደርግም: አይቀበልም: ወይም አይሰጥም:

4ሐ3) በተጨማሪ በ ክፍል 2 የሚሠሩና የተቀጠሩ በፍትሓብሔር ወይም በወንጀል ፍርድ ቤት ተከስሶ (ክፍል 3) ሊፈረድበት ይችላል::
ማንኛዉም አግባብ ያለዉ (standing) ሰዉ ወይም ድርጂት ሌላን ሰዉ ወይም ድርጂትን አግባብ ባለዉ ዳኛ ( ክፍል 3) ከስሶ ፍርድ መጠየቅ እና ማግኘት ይችላል::
እነሆ: ማንም ሰዉ በሕግ ፊት እኩል ነዉ::

5) መደምደሚያ

ፋኖ የሚታገለዉ ጉልቻ ለመቀየር አይደለም: መሰረታዉ ለዉጥ ለመስራት እንጂ:: ፋኖ ኢትዮጵያን ማስተዳደር ከጀመረብት ሦስት አመት ቦኋላ ሦስቱም የህዝብ ሕጋዋ መንግሥት ክፍሎች በህዝብ ተመራጭ ይሠራሉ::
በህዝበ-ሕግ መሰረት የማይሠራ ባለሥልጣን: ወታደር ወይም ፖሊስ ወንጀለኛ ነዉ::

የቃላት ትርጉም

ህዝበ-ሕጋዊ መንግሥት (= ዴሞክራሲያዊ መንግሥት)

ህዝብ (ዲምስ በግሪክኛ)

ሕግ = ደምብ

ህዝበ-ሕግ = ህዝብ ለራሱ ጥቅም ያወጣው ደምብ:: (ካንስቲቱሽን በአሜሪካዊ እንግልዝኛ)::

ህዝበ- ሕጋዊ ሥርአት = ዴሞክራሲያዊ ሥርአት::

ህዝበ-ሕጋዊ መንግሥት = ዴሞክራሲያዊ መንግሥት::

ሀጊ: የካቲት 3/2016 ዓም